አማኑኤል አለማየሁ (ደጀና) 02-07-18

# ዜግነት

- ዜግነት ምንድነው?
- ዜግነትን መሰረት ያደረገው ስብስብ መብት ወይንም ሉአላዊነትስ ምንድነው?
- አንዱ ዜግነት ከሌላኛው ዜግነት በምን ይለያል?
- አሁን ያለችዋ ኢትዮጲያስ የነማን አገር ናት የነማሰን አይደለችም እነማንስ ናቸው ዜግነትን የሚወስኑት?

እና የመሳሰሉት ጥያቄዎቸት ያለማቋረጥ በአይምሮየ ሲንከላወሱ አንድ ጠዋት ተነስቼ የእያንዳንዳቸውን ጥቄዎች መንስኤ አሰላሰልኳቸው እና በራሴ የራሴን መልስ ፈልጌ አገኘሁት፡፡ ከላይ ያነሳኋቸውን ጥያቄዎች ከራሴ ኑሮ እድገት ልምድ ጋር እገናዘብኩ አየኋቸው እና በአንዳንድድምዳሜዎች ተገረምኩ ራሴን ወቀስኩ አንዳንዱም አዘንኩ በተለይ አሁንም መጠየቀም መስማትም ማሰብም በማይፈልጉት ባልከፋባቸውም አሳዮኝ፡፡

## ዜግነት እንዴት ይፈጠራል? ዜግነትስ ምንድን ነው?

ፍጡራን ስንባል ከሁሉም ቅድሚያ የምንሰጠው የፀጋወች (resources) ባለቤትነትን ማረጋገጥ ነው፡፡ ለምሳሌ ውሾች ምግብ ብንሰጣቸው አጠገባቸው ያለ ውሻ የተሰጣቸው ምግብ ላይ እንዳይደርስ በቻሉት ሁሉ ይከላከላሉ አቅሙ ያላቸው ከመሰላቸው በጉልበታቸው ከተማመኑ ደግሞ ባለቤቱን አባረው የጎረቤታቸውን ምግብ ይነጥቃሉ፡፡ አንበሶችም ለየት ባለ መንገድ አጠገባቸው ላለ ምግብ ሳይሆን ግዛታቸው ይከልሉና በዚህ በከለሉት ግዛት ውስጥ ማንም ተቀናቃኝ አዳኝ አንበሳ እንዳይመጣ በማድረግ በዚህ በከለሉት ግዛት ውስጥ የሚገኘውን መታደን የሚችለውን ሁሉ ባለቤትነታቸውን ያውጃሉ፡፡ ልክ እንደ ሌሎች እንስሳትም ይህን ድንበራቸውን ጥሶ ለመግባት የሚፈልግ ማንኛውም የጎረቤት አንበሳ ወይም ተሸናፊ ሆኖ ወይ አሸንፎ ወይንም በስርቆት ካልሆነ በስተቀር በዚህ በተከለለ የአንዱ አንበሳ ቤተሰብ ውስጥ መግባትና ማደን የሚያስከትለውን መዘዝ ስለሚያውቀው ድንበር ሲጥስ አስቀድሞ ማሰብንና የመጠንቀቅን ስራ ይሰጡታል፡፡

ይህ የተከለለ ግዛት ከቤተሰብ ወደ ቤተሰብ ይሸጋገራል እንደ ቤተሰቡ ጉልበትና ብዛት ደግሞ ይሰፋል ይጠባል፡፡ በዚህ በተከለለ ግዛት ውስጥ የአንበሳ ቤተሰብ ሀ ቢኖር እና የመጥቀሱ ወይንም የመጥራቱ እድል ቢሰጠን የአንበሳ ቤተሰብ ሀ ግዛት ብለን እንጠራዋለን አንበሶችም በሽታ ለይተው የማን እንደሆነ ሰለሚውቁት ከድንበራቸው ጋር ኩታ ገጠም የሆነውን ለይተው ወይ በጋብቻ ወይንም በመሸነፍ ወይም በማሸነፍ ይቀላቀላሉ እንጅ በዘፈቀደ በጋጠወጥነት ድንበር አይጥሱም፡፡

ወደ ሰው ልጅ ልመለስ ልክ እንደ እንስሳት በተለይም እንደ አንበሳና እንደመሳሰሉት ነገር ግን እጅግ ዘመናዊ በማድረግና ከእንሰሶች በላይ ያላቸውን ሃይለኛ የጦር መሳርያ ማለትም ማሰብን የመሰለ እጅግ አውዳሚ ክህሎት በመጠቀምና አጠቃቀሙንም በሳይንስና ምርምር በጥልቀት በማሳደግ እንደ መሳርያ ተጠቅሞ ግዛት (ይዞታ) የሚገነባና በምናብ የተሳለ በሳይንስ ተደግፎ ደግሞ በያንዳንዱ የግዛት ዳርድንበር ላይ ክልከላውን የሚያሳይ ችካል የተቸከለበት ወይን የመልክአ ምድራዊ ጥቅስ (coordinate) የተቀመጠበት ንብረትነቱ የማን እደሆነ የሚታወቅ ግዛት አበጅቷል፡፡ ይህ የተበጀው ግዛት በውስጡ ያሉትን እጅግ ከፍተኛ ዋጋ ያወጣሉ የሚባሉትን የተፈጥሮ ሃብቶችን ብቻ ሳይሆን በውስጡ ያሉትን እንስሳት ጭምር በተለይ የሰው ልጅን በባለቤትነትና በንብረትነቱ የያዘ

ነው፡፡ ሁሉም የግዛት ክልሎች የተመሰረቱትም የተስፋፉትም የተፈጥሮ ሃብቶችንና የሰው ልጆችን ለመቆጣጠር ብሎም ለመግዛት ነው፡፡ አንደ ጉልበተኛ ማለትም የመግደል አቅም ያላቸው የጦር መሳርያዎችን እነዚህን የጦር መሳርዎች መጠቀም የሚችሉ የተማሩ (የሰለጠኑ) በአስተሳሰብም ይሁን በእውን የአስማሪያቸው (የአሰሪያቸው) ባርያዎች መሆናቸውን ለራሳቸው ያሳመኑ ሲጠሯቸው አቤት ሲልኳቸው ወዴት ብቻ የሚያውቁ ታዛዥ ታማኞችን የያዘና የያዘው የመግደል አቅም እስኪዳከም ድረስ የቻለውን ግዛት ይይዝና “የእሱ” ግዛት ተብሎ ይሰየምለታል፡፡ ስያሜው በግለሰቡ ስም እንኳን ባይሆን የመሰየሙንም ይሁን ስያሜውን የመቀየር መብት ግን የዚህ የጉልበተኛው ስልጣን ነው፡፡

በአፍሪካ እና የኤሲያ፣ በመሳሰሉት አህጉራት አነዚህ ከላይ የጠቀስኳቸውን ግዛቴ ነው ብሎ የማስመር መብቱ እንኳን ሳይቀር የተነፈጉ ተገዥዎች ናቸው፡፡ የግዛት መስመራቸወንና ስያሚያቸውን እንደ አበዛኛዎቹ ከሆነ በቀጥታ እነደ ኢትዮጲያ ዓይነት አገርን ደግሞ በተዘዋዋሪ ጫና በመፍጠር በዚህ የሚፈጠረው ግዛት ውስጥ እነማን ወይም የትኞች ህዝቦች (ተመሳሳይ ቋንቋና ባል ያላቸው) ለሁለት ተከፍለው በማ እና በማ ስር መስፈር፣ መሰየም፣ መገዛት እዳባቸው የወሰኑት ከሩቅ ሩቅ አገር የመጡ የራሳቸወን ግዛቶች አሽከሮችቸውን አጨፋጭፈው በተቻለ መጠን ብሄር አገርን (nation states) አቋቁመው የጨረሱት ቅኝ ገዥ አውሮፓዎች ናቸው፡፡ እንዲሁ ለጨረፍታ ተመልሸ ለማየት ወደ አፍሪካ መጥተው በማን ስር መገዛት እንዳለብን ማን ተብለን መጠራት እዳለብን፣ ዜግነታችን የት መሆን እንዳበት እና ከተቻለም ምን ቋንቋ መናገር እንለብን የውሱኑልን ወየንም የወሰኑብን በቅርቡ በ19ኛው ክፈለ ዘመን ማለቂያ ወይንም በ20ኛው ክ/ዘመን መባቻ አሁን በቅርቡ ነው፡፡

ከአፍሪካ እና ከኢሲያ የከፋው የደቡብአሜሪካ አገሮች ጉዳዮ እንኳን ቢሆነም ከሁሉም የከፋው ደግሞ የሰሜን አሜሪካና የአውስትራሊያ ነው፡፡ በአውስትራሊያ፣ ኒውዚላንድና፣ አሜሪካ ካናዳ በመሳሰሉት አገሮች ስናይ ጭራሽ በመሬቱ በአፈሩ በወንዙ በተራራው ልክ አንደ ሌሎች ፍጡሮች ይኖሩ የነበሩት ሰዎች ከአፈሩ ከተፈጥሮ ሃብቱ በታች ናቸው አያስፈልጉም እነሱንስ ተገዥ ከማድረግ ከአገራችን ተገዥዎ አስገብን ብንገዛ ይሻለና እነዚህ ከአፈሩ ጋ ያገኘናቸው አፈር ስር እንቅበራቸው የሚተርፉም ካሉበሂደት አፈር ይብላቸው ብው አዲስ ለምድሩ እንግዳ የሆኑ ከየትና የት ከመጫኛዎቻቸው፣ ከቀስቶቻቸው (ጦር መሳርያዎቻቸው)፣ ከማብሰያዎቻቸው ባጠቃላይ ከቤትና ከመስክ እቃዎቻቸው ጋር በጀልባ ጭነው ከአውሮፓ (ከገዥዎች አህጉር) ወደ አዲሱ ምድር አስፍረው መገዛት የለመዱትን “ብዙ ተባዙ ግዛታችንን ሙሉዋት” ብለው ከላይ የጠቀስኳቸውን እና ተመሳሳይ አገሮችን በነባር ህዝቦች እልቂት ላይ አቀኑ አና መግዛት ቀጠሉ፡፡

በዚህ መንገድ የተያዘ ግዛት ልክ እንደአንበሶቹ የግዛቱን ድንበር ያስምርና በዚህ ይዞታየ ውስጥ የሚኖረው የተፈጥሮ ሃብተና ፍጥረት የኔ ነው በማለትበተለይ ሰውን ነጥሎ ዜጋ ይለዋል፡፡

ይህ በጉልበት በገዥዎች ፈቃድ የተከለለ፣ ተገዥዎች የታሰሩበት፣ ድንበር የተበጀለት የሰው ልጅ ሊኖረው ይችል የነበረውን ስፋት ያለውን የምድር እንቅስቃሴ የገደበ፣ ጠበብ ጠበብ ባሉ የበሬ ግንባር በሚያክሉ የመሬት ስፋቶች የተወሰነውን ይዞታ አገር ብው ስም ሰጥተው ምልክት አበጅተው መግዛት ሰውም መገዛትን ተያያዝነው፡፡ የየምንገዛበት ገዥዎቻችን በሞያተኞቻቸው አማካኝት ቁጭ ብለው አስበው ቀለማትን ደርድረው ጨርቅ ላይ ይስሉና ለዚህ ለግዛታቸው መለያ አርማ አበጅተው ሰጡን፡፡ ቅጭ ብው በጥቂት ሰዎች የተቀረፀውን እና የተመረጠውን ቀለም ጨርቅ ላይ ስለው ዘንግ ላይ ሰቅለው አምልኩት ብለው ሰጡን እኛም በሰጡን ትእዛዝ መሰረት አመለክነው አና ገዥዎቻችን ፀብ ሲያምራቸው ቁጣ ቁጣ ሲላቸው በአምሳያ መገዛታችን የተፈጠረውንና ያመለክነውን ጨርቅ ከፊት ለፊታችን እያሳዮ ወደ ሚያዘጋጁት ወይንም በሌላ የጎረቤትም ይሁን ከሩቅ መጤ ጎረምሳ ወደተዘጋጀው እሳት ግቡ ሲሉን ጨርቁን ብለን እንሞታለን እነሱ እሳቱ ከሚነድበት የእልቂት አውድማ በጣም ርቀው ቤተ

መንግስታቸው ውስጥ ተደላድለው በምቾት "እየተሰቃዩ" የመጀመርያም የመጨረሻም ተቀጣጥዮች ያደርጉና፡፡ ለዚህ የመሞት የመጠበስ የመቀቀል ውለታን፣ ለጥሩ ታዛዥነታችን ተገዥነታችን ትልቁ ሽልማት ምርጥ ዜጎች የሚል ተቀፅላ ይሰጡንና ሌሎች ተከታዮች እኛን አይተው እንዲበዙ፣ እንዲበረክቱ፣ ቆራጥ እንዲሆኑ፣ በአደባባይ ምርጦቻቸውን ያስተዋውቃሉ እና እኛ በዚህኛው ገዥ በኩል ሆነን ባለንጀሮቻችን በዛኛው ገዥ ስር ሆነው ለየ ገዥዎቻንን ታማኝነት ስንል እንሞሻላለቅና በየ ገዥዎችን በኩል የተሰጠንን ዜግነት (ባርነት) ለመጠበቅ ብለን እንገዳደላለን፡፡

ስለዚህ ዜግነት ገዥዎች ከልለው በያዙት እና በገዙት ግዛት በዳር ድንበራቸው ውስጥ ለሚኖር የሰው ፍጡር የተሰጠ ንብረትነቱ የማን እንደሆነ የሚገልፅ ስያሜ (ታፔላ፣ ወረቀት፣ አዋጅ ወይንም መጠርያ ምልክት ነው)፡፡ በዚህ መንገድ ተጀመሮ አሁን ባለንበት ዘመን የሰው ልጅ ስልጣኔ በማደጉ ምክንያት አንድን ሰው ንብረትነቱ የማን መሆን እንደሚፈልግ ውሱንም ቢሆን የመምረጥ መብት ይሰጠዋል፡፡ ለምሳሌ ፡-

1. በአንድ ራሱን ቡድን አድርጎ ስሜት መፍጠር በሚችል ልሂቅ የሚመራ የሰዎች ስብስብ ወይ በጉልበቱ ወይንም በጩሀቱ ይሰባሰብና ***<u>ህዝብ ውሳኔ</u>*** በመጥራት የእያዳንዱን አባል የየትኛው ልሂቅ በርያ (ተገዥ) መሆን እንዳለበን እንዲወስን ሊደረግ ይችላ፡፡ ልክ እንደ ካታሎኒያ ስፐይን፣ እነደ ምስራቅ ቲሞር፣እነደ ደቡብ ሱዳን ወዘተ.
2. ሌላኛው ደግሞ አንዱ ልሂቅ (elite) ይነሳና እነዲሁ አሽከሮች ያሰባስብና ራሱን ከዛኛው ግዛት ይነጥልና የነጣዮ ልሂቅ ንብረት የሆነ ግዛት ያቋቁማል፡፡ ይህ አይት ግዛት አወቃቀር አብዛኛው የሚለየው በደመነብስ ወይ በወል የሚወስን መሆኑ ነው፡፡ ምሳሌ እንደ ኤሪትራ፣ እንደ የባልካን አገሮች አይነት፡፡
3. ሶስተኛው እኔ አጅጉ የሚገርመኝ አይነት ዜግነት(ተገዥነት) ነው፡፡ አሁን ባለንበት ስልጡን ዘመን አንድ ግለሰብ በአንድ ወይ በሌላ ምክንያት እትብቱ ከተቀበረበት አካባቢ(ግዛት) ይርቅና እሱን ከማይመስሉና ብዙም ከማያውቃቸው ሰዎች ቀየ ሄዶ ወይም አለቃቀወሶ ወይን ገንዘብ ከፍ የሚጠይቁትን ጥየያቄ የወደፊት ገዠዎቹን በሚያስደስት መልኩ ጥያቄዎችንውን መልስ እየመለሰ የተወለደበትን አገር አሳዳሪ ተገዥ ከመሆን የአዲሶቹ ተገዥ ለመሆን በብዙ ስለት የሚገኝ ለየት መገዛት እዳለበት የሚወስንበት የዜግነት ሂደት ነው፡፡ (this is called naturalized citezenship)

ስለዚህ ዜግነት ማለት በየትኛው ግዛት/ግዛቶች ውስጥ እየተገዛህ እደሆነ የሚያሳይ መታወቂያ (ፓስፖርት) ነው፡፡

በነገራችን ላይ በማን ስር እንደምንገዛ የሚያሳየው መለያ መታወቂዎችን በስተጀርባ ሄደን ፖለቲከውን ስናጠና ምን ዓይነት ገዥ ስር እንዳለን ይነግረናል፡፡

አንዳንዱ ፓስፖርት (መታወቂ) ዜግነት እንኳን እንደሰው እንደ እንስሳ እረ እንደ ሳር ቅጠሉ አንኳን የመኖር መብት አይሰጥ፡፡ አንዳንዱ ደግሞ አያስርህም ሃብት አለው ይቀልብሃል ነገር ግን እንድታስብ አይፈቅልህም፡፡ ሌላው ደግሞ ታስባለህ ትባላለህ ነገር ግን መስመር ተሰምሮልህ ከተሰመረው መስመር ውልፍጥ ስትል ይቀዝፍሃል፡፡  የዚህኛው ለየት የሚያረገው ሌሎቹ የሚያደርጉትን ሁሉ አድርጎ የሰለቸው ሰለሆነ ትንሽ የርሀራሄ ወይም መሞቱ ላይቀር ለምን እገድለዋለሁ የሚል ተፈጥሮዊ ሞት እስከትሞት ይጠብቅሃል፡፡ የሰው ልጅ እኩል ነው ይልሃል ግን እኩል አለመሆንህን ሰላሳመነህ አትከራከርም፣ አትቃወምም እንዲያውም ከሌሎች ገዥውች (ዜግነት ሰጪ እና ነሽዎች) በተሻለ መንገድ ስለሚይዝህ በማንኛው መንገድ ብትሞትለት ትመኛለህ፡፡ የኖርዲክ እና አብዛኛዎች የአውሮፓ አገሮች መመልከት ጥሩ ነው፣ በተለይ በንጉሳዊ ስርዓት የሚተዳደሩት፡፡ በነዚህ አገሮች ሰው እኩል ነው ይሉሃል ነገር ግን ሰው አኩል አለመሆኑን ከስርአታቸው ታየዋለህ ንጉሱ ወይም ንግስቲቱ ከሰው

በላይ ከፈጣሪ በታች መሆናቸውን አምኖ የተቀበለ ዜጋ ስለፈጠሩ ስጋት የለባቸውም፡፡ ልኡሉ አራስ ሆኖ ከእናቱ ማህፀን ሲወጣ ከሁሉም ይበልጣል ከአባቱ ከንጉሱ በስተቀር፡፡

ስለዚህ ዜግነታችን የጭቆናችን መጠን ለያይቶ የሚነግረን የየትኛው ድሃ እና የየትኛው ሃብታም አህዮች መሆናችንን ማሳወቅያ ካርዳችን ነው፡፡

## ህዝብ ምንድን ነው? እንዴት ነው የሚፈጠረው?

ህዝብ ዝም ብሎ የግለሰቦች ስብስብ ወይንም ጥርቅምም አይደለም፡፡ አንድ ህዝብ ውስጥ ያሉ ሰዎች ትግባቦት፣ማህበራዊ ትስስር፣የጋራ እሴት፣ተቀራራቢ አሰፋፈር፣ የጋራ ስነልቦና፣ ኢኮኖሚያዊ ትስስር ወዘተ ያለው ፖለቲካዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ማንነት የሆነ የሰዎች ማህበር ወይንም ማህበረሰብ ነው፡፡

ህዝብ በዘር ሃረግ ወይን በትውልድ አይመሰረትም፡፡ ህዝብ የአንድ አባት አና የአንድ እናት ልጅ አይደለም፡፡ ለምሳሌ የአማራ ህዝብ የአንድ አባትና የአንድ እናት ልጆች ያቋቋሙት ስብስብ ማህበረሰብ አይደለም፡፡ የትግራይ ህዝብ ፣የኦሮሞ ህዝብ፣ የሶማሌ፣ የአፋር ወዘተ ህዝቦች በተመሳሳይ የአንድ ባልና ሚስት ልጆች የፈጠሩዋቸው ማህበረሰብ (ብሄሮች) አይደሉም፡፡

ህዝብ፣ ብሄር ወይን ብሄረሰብ ሊፈጠር የሚችለው በተጎራባች በጠባብ ቦታ የተፈጠረ የተቀራረበ የማህበረሰባዊ ግንኙነት እየተስፋፋ እንዲሄድ በሚያደርጉ የማበረሰባዊ ማለትም የባህል የቋንቋ እንዲሁም የኢኮኖሚ ማለትም የግብይት መስተጋብሮች እንዲሁም የፖለቲካ ግጭቶች እና መስፋፋቶች አንድን ህዝብ ይፈጥሩታል፡፡

በግብይት ቋንቋ ይስፋፋል፣ በማህበረሰባዊ ምግባሮች በተመሳሳይ ባህልም ቋንቋም ይስፋፋል በተጨማሪም በጦርነቶች መግዛት የሚፈልጉና ሰፋፊ ቦታዎችን ማስገበርና ሰፋፊ የተፈጥሮ ሃብትን መቆጣጠር የሚፈልጉ ገዥዎች በጦርነት ሲስፋፉ ቋንቋቸውንና ባህላቸውን በተስፋፉበት ህዝብ ላይ ይጭኑና አዲስ ግዛታቸው ቋንቋቸውን እንዲናገር ያደርጉታል፡፡

ስለዚህ ህዝብ የሚፈጠረው በመስተጋብር በግጭት (social, economic, political interacions)እንጂ በዘረመል ወይንም በዘር ሃረግ አይደለም፡፡ አንድ ህዝብ አንድ አይነት ቋንቋ ሲናገር ባህል እና የተቀራረበ ስነልቦና በግብይትና በተመሳሳይ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ሲያጠናክር ብሄር ወይንም ብሄረሰብ ሆኖ ይፈጠራል፡፡

በዚህ አይነት የተፈጠረ ህዝብ በ19ኛ ክፍለ ዘመን በተፈጠረ የቅኝ ግዛት ልዩ ክስተት የአለማችን ብዙ አገሮች ሲፈጠሩ በአንድ፣ በሁለት ወይንም ከዛ በላይ በሆኑ አገሮች ውስጥ ሊከፋፈል ይችላል፡፡ የዓፋር ህዝብ በሶስት አገሮች ውስጥ የሶማሊያ ህዝብ በተመሳሳይ በሶስት አገሮ የትግራይ ህዝብ በሁለት አገሮች ወዘተ እንዲኖሩ ምክንያት ሆኗል፡፡

## ሉአላዊነት ምንድን ነው?

ብዙ ባንዲራ የሰቀሉና ገዥ ነን ብለው ያሙኑም የነሱ አፈቀላጤ መሁራን ስለሉአላዊነት ስለየስብስብ (የወል) መብት ሲያወሩ እሰማለሁ፡፡ ሉአላዊነት ምን ማለት ነው ብየ ራሴን እጠይቅና በይደር እያያዝኩ አሁን እዚህ ደረጃ ስደርስ ግን ማሳደር አቃተኝ፡፡ ምክንያቱም ዜግነት ማለት የየትኛው ገዥ ተገዥ እንደሆንኩ የማውቅበት እንደሆነ ካረጋገጥኩ በኋላ ተገዥዎቻችና ገዥዎችስ የጋራ የሆነ ነገር ምን አለን ብየ ስጠይቅ ሉአላዊነት የሚል ስያሜና አርእስት መጣልኝ፡፡ ሳስበው ሉአላዊነት የሚለው ቃል በርግጥ የኛና የግዥዎቻችን የጋራ ንብረት (አርእስት) ነው፡፡ ነገር ግን ሉአላዊነት ነፃነትን፣ በራስ መወሰንን የሚያመለክት ይመስላል፤ ከሆነስ በርግጥ ነፃ ነን?

የድሮውን ትተን አሁን ባለንበት ዘመን እውን እኛና ገዥዎቻችን እንዲሁም በገዥነትና በተገዥነት የምንኖርት የተከለለውን በረታችን ውስጥ ሉአላዊ (ነፃ) መብት ያለን ነን የኛስ ይቅር ገዥዎቻችንስ በቻሉት ያክል እኛ ላይ ጉልበተኞች ይሁኑ እንጂ እነሱስ ከሌሎች ገዥዎች ጋር ሲነፃፀሩ ቀና ብለው መሄድ የሚችሉ ቀጥ ያለ አንገት (ማለት ጭንቅላታቸውን የሚሸከም አቅም ያለው) አላቸው ወይንስ አንገታቸው ቀና የሚለው፣ ቀጥ የሚለው እኛን እንደፈለጉ በሚያደርጉበት ግዛት ውስጥ ብቻ ነው? እነዚህ ከላይ ያነሳሁዋቸውን ጥያቄዎች ከፖለቲካም ወጣ ባለ እና አሁን ካለንበት አለማቀፍ ኢኮኖሚና፣ አለማቀፍ ፋይናንስ ጋር በማያያዝ ለመመለስ እሞክራለሁ፡፡

እውን ሉአላዊ መንግስት ነን ብለው ራሳቸውን የሚጠሩት ሉአላዊ መንግስት ናቸው? ወይንስ የእኛ የተገዥዎችን የግዛት ዘመን ለማራዘም እንዲያስችላቸው ሃያላን መስለው ለመታየት ነው እረ እኛ ሉአላዊ መንግስት ነን ሉአላዊ አገር ነን በለው የሚነግሩን ?

አንድ መንግስት የበጀት ጉድለት ሲያጋጥመው፣ የሚገነባ ፕሮጀክት ሲኖረውቁሳቁስ መግዛት ሲያምረውና ወዘተ አበዳሪ ጋ ይሄድና ብር እንዲያበድረው ይጠይቀዋል፡፡ አበዳሪዎቹ ብዙ ጊዜ መንግስታት አይደሉም የፋይናንስ ተቋማት ማለትም ትላልቅ ባንኮችናየፋይናንስ ኮርፖሬሽኖች ናቸው፡፡ እነዚህ ተቋማት ዋስትና ይፈልጋሉ የሚቀርብላቸው ዋስትናም ተራ ዋስትና አይደለም ፖለቲካዊ ዋሰትና ነው፡፡ ይህ ፓለቲካዊ ዋስትና የሉአላዊነት ዋስትና (sovereign guarantee) ተብሎ ይጠራል፡፡ይህ የሉአላዊነት ዋስትና አገርን፣ መንግስትነትን፣ ዜጋንና ሳር ቅጠሉን በሞላ በዋስትናነት አስይዞ መበደር ማለት ነው፡፡ ተበዳሪው አገር ለአበዳሪው ኩባንያ፣ ባንክ ወይንም ኮርፖሬሽን እዳውን መክፈል ላይ ዳተኝነት ቢያሳይ፣ ቢያቅማማ ወይንም ነፃነቴን እፈልጋለሁ አይነት የሞኝ ጨዋታ ቢፈልግ እስከ አፍንጫቸው የታጠቁት የምዕራብ መንግስታት እና የፈለጉትን ቦታ በፈለጉት ሴከንድ ማደባየት በሚችለው የጦር ሰራዊታቸው ይሰፍሩበታል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ሰበብ ይፈለግለትና ለዘለአለሙ ድምጥማጡን ያጠፉታል፡፡

አሁን ያሉት መንግስት ነፃ መንግስታት፣ ከብድር የፀዱ፣ በውስጥ የፋይናንስ ጉዳያቸው ላይ የሚወስኑ መንግሰታት የመሆን መብትም ያላቸውም፡፡ ለዚህ በጣም ጥሩ ምሳሌ ሊቢያ ናት፡፡ ሊቢያ የራሱዋ የሆነ የወርቅ ዲናር ወይንም በወርቅ ዋስትና የተደገፈ ገንዘብ ለመስራትና ግብይትን በወርቅ ዋስትና በተደገፈ ገንዘብ ለማቀላጠፍና ዋስትና ባለው መንገድ ለማድረግ ማሰቧ የአለማችን የገንዘብ አፄዎች ተረባርበውባት እጅግ ሰላማዊ የነበረችዋ አገር አሁን ወደ የምናያት ሲኦል ቀይረዋታል፡፡

ሊቢያ እዳ አልነበራትም፣ ሊቢያ በጀመረችበት መንገድ ብትቀጥል ኖሮ እነዚህ የገንዘብ አማልእክት (gods of Money) የማይቆጣጠሩትና በፈለጉበት ጊዜ ዋጋው እንዲወርድ (inflate) የሚያደርጉት ገንዘብ ተጠቃሚ ስለምትሆን ለነፃነት ፈገላጊ መንግስታት፣ እዳቸውን መክፈል ለሚችሉ መንግስታት አርአያ እንዳትሆን በጊዜ ሊቢያን ማጥፋት አስፈላጊ ነበርና አደረጉት፡፡ ነፃ፣ ለኡላዊ መንግስታት በአለማችን የሉም ከዚህ በኋላ ይኖራሉ ተብሎ አይገመትም፡፡ ነፃ መንግስት በሌሉበት ነፃ ዜጎች አይታሰብም ምክንያቱም ነፃ ዜጎች የነፃ መንግስታት

ውጤቱች ናቸው፡፡ ከላይ በመግቢያየ ዜግነት የየትኛው መንግስት ብሎም ገዥ ባርዎች መሆናችን ማሳወቅያ መታወቂ (ፓስፖርት) ነው ብየ ነበር፡፡

እነዚህ ሉአላዊነት የሌላቸው መንግስታት እኛን የሚፈልጉን ግብር እንድንከፈልላቸው ነው፡፡ ቅንጡ መኪኖች ይገዛሉ፣ በቅንጦት ይኖራሉ፣ የፈለጉትን ያክል ገንዘብ ይዘርፉና አውሮፓና አሜሪካ (ጌቶቻቸው ቤት) ያሰቀምጣሉ ከዛ እዳውን ወደ እያዳንዳችን በታክስ፣ በዋጋ ግሽበት (inflation) መልክ ይገፉና እድሜ ልካችን በእስረኝነት እንድንቀጥል ያረጋሉ፡፡

በየኪሳችን እድንይዘው በደሞዝ መልክ የሚሰጡን የወረቀት ኖት (ብር፣ ዶላር ወዘተ) እንኳን በየቀኑ የምንኖረው በአንድ አዋጅ ላይ የተንጠለጠለ ሂወት (ኑሮ) እንዳለንና እጅግ በሚዘገንን ባርነት ውስጥ የምንኖር እስረኞች እንደሆን ማሳያ የባርነት ለኑሮ (slavery for survival) መመገቢያ ኩፖናችን ነው፡፡ ሲሰጡን እንበላላለን ሲከለክሉን እንራባለን ከዛም እንሞታልን፡፡

መንግስታት ሉአላዊ አይደሉም በትልልቅ ባለጡንቻ አበዳሪዎች ቁጥጥር ስርያሉ እስረኞች ናቸው እና ዜጎች ደግሞ በመንግስታቶቻችን ስር ጠበቅ ተደርገን የታሰርን እስረኞች ነን፡፡ በመሆኑም ሉአላዊ ሰዎች አይደለንም ልአላዊነት በሌላቸው እየተዳደሩ ሉአላዊ መሆን አይችልምና፡፡

## <u>አንዱ ዜግነት ከሌላኛው ዜግት በምን ይለያል</u>?

ዓለማችን ላይ እጅግ ብዙ ሰዎች ዜግነታችውን መሰረት አድርገው እኔ ከዚህ አገር በመወለዴ እኮራለሁ የዚህ አካባቢ በመሆኑ እኮራለሁ፣ እመካለሁ ወዘተ ይላሉ፡፡ ከብዙ ሰዎች አባባል ስነሳ ኢትዮጺያዊ በመሆኔ እኮራለሁ፣ ኬንያዊ በመሆኑ እኮራለሁ፣ ጀርመናዊ በመሆኔ እኮራለሁ ወዘተ በመሆኔ እኮራለሁ እየተባለ ዓለም ላይ ያሉ አገሮች በሙሉ የዛ የተለየ ድንበር የተበጀለት አገር ዜጋ /ባርያ/ በመሆን የሚኮሩ ሰዎች ይፈጥራሉ፡፡ ይህን አይነት ስሜት ለመፍጠር ደግሞ ትምህርትን በተለይ ደግሞ የታሪክ ትምህርትን፣ የስነሰው ሳይንስን፣ ማህበራዊ ሳይንስን፣ ፖለቲካዊ ሳይነስን ወዘተ በመጠቀም ይቀርፁናል፡፡ በተለይ ታሪክን እንደ ማስፈራርያ ይጠቀሙና ከህፃንነታችን ጀምረው በዚህ ቅኝት እየደጋገሙ በመጠቅጠቅ ከዚህ ከጠባብና ገዥዎች በስግብግብነታቸውሊሻሙ ሲሉ፣ የሰው ልጅን በባሪያነት ለማሳደር ሲሉ ተሸምተው የፈጠሩትን ዳርድንበር አምለኪ እንድንሆን ይቀርፁናል፡፡ በዚህ ገና ከህፃንነታችን ጀምሮ እነዲህ እየተጠቀጠቅንተቀርፀን ያደግን ዜጎች በፈጣሪ የተሰጠንንሰውነት (ሰው መሆን) አስረክበን የማንነት /የዜግነት/ ፀጋ ብቻ እነዳለን አድርጎ በማሰብ ስለ አገር፣ግዛት ስላደረጉን የገዥዎችድጋግመው በመንገር ድንበር አማላኪ ምግዛት ወዳጆች እነድንሆንና አገር ሲሉን፣ ዝራፍ ሲሉእንሞታለን እንገድላለን ወይንም ለመሞትና ለመግደል እንዘጋጃለን፡፡

እያንዳንዱ ሰው በህሊናው የሚፈጥራቸው የተለጣዮ የሚባሉ አገሮች አሉት በነዚህ በፈጠራቸው ምስሎች ውስጥ ሆኖ የኔ ከሌላኛው የሱነት ወይንም ዜግነት ይበልጣል ወይንም ያንሳል ይላል፡፡ የኔ ያንሳል ብሎ የሚያስበው ምንም እንኳን የተፈጠረበትን አገር አምላኪ ለመምሰል ቢሞክር የሚሰጠውን ፓስፖርት የተወለደበት አገርን የሚያሳየውን የማንነት መታወቂያ የርግማን ማዓት አውርዱ፣ አውግዞ ሌላ ማንነት ሌላ መታወቂ ይይዝና የዚህ የተፈጠረበት ሳይሆን ከተፈጠረበት የበለጠ ነው ብሎ ያመነበትን ሌላ ማንነት ሌላ ዜግነት ብዙ ከፍሎብዙ አውግዞ ብዙ ተራግሞ ያገኛል ወይንም ለማግኘት ይጥራል፡፡

ስለዚህ ለዚህ ዜግነቱን ለቀየረ ሰው ይህ ዜግነት አብዛኛው ዜግነት ወይም የአሁኑ አዲሱ ዜግነት ከነባሩና ከተፈጠረበት ዜግነት ይበልጣል ማለት ነው፡፡

ስለሆነም ዜግነት ይበላለጣል በየሰው ምርጫ መሰረት የሚወሰን ቢሆንም አንዳንዱ ዜግነት ወደ ሲኦል (ሲኦል ካለ) የተጠጋ ኑሮ፣ ሂወት፣ ስጋት ጭንቀት እየሰጠህ እንድትሞትለት በየጊዜው ይጎተጉትሃል፡፡ ወታደር ሁን መሳርያ ያዝ፣ ጠብቀኝ ለኔ ስትል ሙት የሚል ብዙ ትምህርት ስልጠና እየሰጠ እሳት ላይ መማገድን ከመንግስት ወርዶ ወርዶ የጎረምሳ አለቆች፣ የጎበዝ አለቆች ደረጃ ይደርስና የእንትና አሽከሮች እየተባባሉ መጠፋፋትን መገዳደልን ድረስ ያስከትላሉ፡፡

አንዳንዶች በተለይ የታደሉት ዜግነቶች ከዜጋቸው የሚፈልጉት ግብር እንዲከፍላቸው ምቾታቸውን እዲጠብቅላቸው እንጂ በዋናነት እንዲሞትላቸው አይደለም፡፡ ሰለሆነም እንዲማር፣ በበለጠ አምራች እንዲሆን ብዙ ገቢ እንዲያስገባ ይፈለጉታ፡፡ ብዙ ገቢ የሚያስገኝ ሆኖ ብዙ ግብር ከፋይ ሆኖ እስከተቀመጠ ድረስ ይንከባከቡታል ምክንያቱም የገቢያቸው ምንጭ ነውና፡፡ እንደዚህ ዓይነት ዜግነቶች በርግጥ የሚያስቀኑ በአሁኒቱ ዓለም በብዛት የሚይገኙ እጅግ የተሻሉ ዜግነቶች ናቸው፡፡

ስለዚህ ዜግነቶች ይበላለጣሉ፣ ይለያያሉ

- ወደ ሞት አፋፍ ሁሌ የሚገፉህ በረባ ባለረባ ጦርነት እያወጁ ሁሌም ስጋት ውስጥ እንድትኖር የሚያረጉህ
- እስካመለከን ድረስ አየቀለብን የምናስቀምጥህ ግኡዝ ነህ የሚሉ
- ግብር እነድትከፍላቸው የሚነከባከቡህ ጤናህን የሚጠብቁልህ እንዳታምፅ የማያስርቡህ

  ወዘተ እንደየ አስተዳደራቸው ይለያያሉ፡፡

__አሁን ያለችዋ ኢትዮጲያ የማን ናት? የማንስ አይደለችም?__

አገር የማን ነው የሚለው ከላይ በገለፅኳቸው ምክንያቶች ማለትም ቅድሚያ የአበዳሪዎች ቀጥሎ የአካባቢ መንግሰት (ገዥዎች) ናት፡፡ ነገር ግን ዜጋን (ተገዥን) ደግሞ መሬት ላይ ማስቀመጥ ስላለብኝ ከላይ ከጠቀስኳቸው ቀጥሎ እስኪሞት ድረስ ማቆያ ማበጀት ስላለብኝ እስኪሞት ድረስ መቆያውን ለማመላከት ያነሳሁት ጥያቄ ነው፡፡

በኢትዮጲያ ህገመንግስት መሰረት አሁን ያለችዋ ኢትዮጲያ በኢትዮጲያ ውስጥ የብሄረሰቦች ንብረት ናት፡፡ የኢትዮጲያ ሉአላዊ ባለስልጣኖች የኢትዮጲያ ብሄር ብሄረሰቦች መሆናቸውን በህገ መንግስቱ መግቢያ ላይ በግልፅ አስፍሯል ፡፡ ኢህአዴግ ኢትዮጲያን የብሄር ብሄረሰቦች ንብረት ናት በማለት አገር ማለት ህዝብ ማለት ነው በማለት አገር የውል (የብዝሃን) ንብረት እንደሆነች አድርጎ ይገለፃታል፡፡

ቀደምት ገዥዎቻችን ደግሞ አገር ማለት የግዛት አንድነት ነው በማለት አገር ማለት ዳርድንበርና በዳርድንበሩ ውስጥ ያለው ሃብት (resource) ነው ብለው ይገልፁዋትና በድንበር ዙርያግጭት እንኳን ሲፈጠር ለዳርድንበርህ ተነስ ይላሉ እንጂ ለህዝብህ ስትል ተነስ አይሉም፡፡

በኔ እይታ ኢትዮጲያ ዳር ድንበር ብቻ አይደለች፣ የወል ንብረትም አይደለችም ምንያቱም የወል ንብረት የማንም አይደለምና፡፡ ሰለዚህ ኢትዮጲያ የእያንዳንዱ ዜጋ ስሜት ወይንም እወቀት ናት፡፡ ኢትዮጲያ ከስሜታችን ስትወጣ፣ ከእውቀታችን ስትወጣ በመግቢያየ አካባቢ እንደገለፅኩት ዜጋው ህሊና ይሸፍትና አገር ጥሎ ይሄዳል ብሎም ዜግነት ይቀይራል፡፡

ስለዚህ ኢትዮጲዊነት ይሁን የሌላ አገር ዜግነት ፓስፖርት ሲሰጠውም ይሁን ፓስፖርት ከማግኘቱ በፊት አራግፎ፣ አውልቆ ሊጥለው ወይ በስሜት ሊለብሰው የሚችል ካባ እንጅ እስከ አሁን እየተነገረን እነደነበረው የማይነካ፣ የማይደፈር፣ ጥያቄ ውስጥ የማይገባ ማንነት አይደለም፡፡

እጅግ ብዙ ሊባሉ የሚችሉ ሰዎች ባንድ ወይንም በሌላ መልኩ ዜግነታቸውን ይቀይራሉ፣ አዲስ ለያዙት ዜግነት ወታደር ይሆናሉ፣ ግብር ይከፍላሉ በአዲሱ ፓስፖርቸው ውስጥ ይቆጠራሉ፡፡ ወደ ነባር ወይንም ወደ ተወለዱበት አገር ሲመጡም ወይን በተለየ ፈቃድ አሊያም በቪዛ በቻ ይገባሉ ልክ አንደ የሌላ አገር ዜጋ ይያዛሉ፡፡

እጅግ ብዙ ሊባል የሚችል ኢትዮጵያዊ ከቻለ የአሜሪካ፣ የካናዳ፣ የአውሮፓ አገሮች ቪዛ ብሎም ዜግነት ለማግኘት የቻለውን ንብረቱን ሃብቱን (ጥሬቱን) አፍስሶ የቻለውን ለኤንባሲ ገብሮ ካልቻለም በሞት በታጠረ የሞት ማሳ (field of death) አቆራርጦ ዜግነት ፍለጋ፣ አገር ቅየራ ይሄዳል በሂደቱም ላይ ስቃይ፣ ሞት ይገጥመዋል፡፡ ከብዙ ውጣውረድና ስቃይ በኋላ የተመኘው አገር ሲደርስ ደግሞ የደረሰበት አገርን ቪዛ ብሎም ዜግነት ፍለጋ የተፈጠረበትን አገርና መንግስት በሚችለው መጥፎ ቃላት ሁሉ ማውገዝ (denouncing his/her natural born citizenship) ይጠበቅበታል ከዛም አዲስ ዜግነት ያገኝና (naturalized citizen) ይሆናል፡፡

ከላይ በገለፅኩት መንገድ ዜግነት የሚቀያየር ከሆነ አውልቀው የሚጥሉት ካባ ከሆነ፣ ስሜት ሲሽፍት የሚጣል ከሆነ፣ ገንዘብ ተከፍሎ የሚገዛ ከሆነ ኢትዮጵያዊነት በተናጠል የምንፈጥረው ስሜት ወይንም ውሳኔ እንጂ የውል ይሁን የድንበር ጉዳይ አይደለም፡፡ እያንዳንዳችን በሚሰማን ስሜትና ስሜታችንና አቅማችን ሊወስደን የቻለውን ርቀት ከሄድን የምንይዘው፣ ግብር የምንከፍልበት ወይንም የምንገዛበት ክልል (አገር) ማሳ መታወቂያ ነው፡፡ አቅም ካጣን፣ ፍላጉት ካጣን ወይንም ከሌላው የተሸል መስሎ ሲሰማን ከአማረጮቹ እኛ የያዝነው ፓስፖርት የተሸለ ሆኖ ከተሰማን ወይንም ለያዝነው ፓስፖርት የተለየ የጠለቀ ፍቅር ካለን ዜግነታችን ጠብቀን እንይዛለን፡፡

ስለዚህ ኢትዮጲያዊነት በእያንዳንዳችን ጭንቅላት በየግላችን መመለስ ያለብን እንጂ በጅምላ ልንመልሰው የሚገባን ጉዳይ አይደለም፡፡ ኢትዮጲያ የኢትዮጲያ ፓስፖርት የያዘና (ዜግነቱን ያልቀየረ ለማለት ነው) ኢትዮጲያ ከምትባው ስእል (image) ጋር ስሜታዊ ትስስር ያላቸው ዜጎች ንብረት ናት፡፡ ከዚህ ውጭ ያሉት ኢትዮጲያዊ ነኝ ብሎ ቢያወራም የሱ ናት ማለት አይደለም፡፡